# <u>አፋልጉኝ</u>

<u>ተፈላጊው ግለሰብ  አቶ በልሁ ማሞ ወንድሜነህ ይባላሉ፡፡</u>

- የአባት ስም- ሻለቃ ማሞ ወንድሜነህ ወልደአማኑዔል፣የእናት ስም- ወ/ሮ አበባዬ ገብሩ ኪዳነ ማርያም
- የትውልድ ቦታ -  ሰሜን ሸዋ ደብረ ብርሀን ከተማ ጠባሴ ሲሆን ዘመኑ 1949ዓ.ም ነው፡፡
- የ1ኛ እና የ2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን  በነገሌ ቦረና አጼ ካሌብ ትምህርት ቤት እና በአዲስ አበባ ኮከብ ጽባህ እና በየነ መርሀድ እንዲሁም በሽመልስ ሀብቴ ትምህርት ቤቶች የተማሩ፣
- ከ1967ዓ.ም እስከ 1968 ዓ.ም ድረስ  በጊዜው መንግስት ባወጣው አዋጅ መሰረት የእድገት በህብረት የስራ እና የትምህርት ዘመቻ ላይ በደቡብ ኢትዮጵያ ቡርጂ ሶያማ በተባለ ቦታ ዘምተው ህዝባዊ ኃላፊነታቸውን የተወጡ ናቸው፡፡
- በመቀጠልም ከ1972ዓ.ም  እስከ  1976ዓ.ም ድረስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የህግ ትምህርት ተከታትለው በማህረግ የተመረቁ ሲሆን፤
- ከ1977ዓ.ም እስከ 1980ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ በኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ጥናት ኢንስቲትዩት እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት የህገ መንግስት አርቃቂ ኮሚሽን ባልደረባ በመሆን የህገ መንግስት የህግ ጉዳዮች ረዳት ኤክስፐርት በመሆን አገልግለዋል፡፡
- በ1980ዓ.ም ለከፍተኛ ትምህርት ተልህኮ ወደ ሕንድ አገር የሄዱ ሲሆን ከዚያ በኃላ ቤተሰቦቻቸው አድራሻቸውን ማግኘት አልቻልንም፡፡የት እና በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ ሳናውቅ ለረጅም ጊዜ ቆይተናል፡፡በተለያየ ጊዜም ያደረግነው በርካታ የመፈለግ ሙከራዎችም ሊሳኩልን አልቻሉም፡፡
- አቶ በልሁ ማሞን ያሉበትን ቦታ እና አድራሻቸውን የሚያውቅ ልበቅን ኢትዮጵያዊ ሁሉ በመጀመሪያ መላ ቤተሰቡ ስለ ትብብራችሁ እያመሰገንን ቤተሰቦቹን ለማግኘት የሚከተሉትን አድራሻዎች መጠቀም የሚችሉ መሆኑን እንገልጻለን፡-
- 1/ ወ/ሮ አበባዬ  ገብሩ ......... ስልክ ቁጥር_________ +251 911 72 04 05
- 2/ ወ/ሮ እንግዳዬጥ ማሞ ....ስልክ ቁጥር————— +251 911 05 76 72
- 3/ አቶ ገነነ ማሞ ..................ስልክ ቁጥር————— +251 941 55 94 58

ወይም በኢሜይል - <u>Geneneethio@gmail.com</u> ብለው ሊያገኙን ይችላሉ፡፡

እህታችን ወ/ሮ በላይነሽ ሰለሞን ነዋሪቷ አሜሪካ ኒውዮርክ የሆነ ለማናቸውም ጥቆማ እና ንግግር ከቤተሰቡ ጋር አብራ ስለምትሰራ የእርሷን አድራሻ መጠቀም ይችላሉ፡፡

<u>ፈላጊ ቤተሰቦቹ፡-</u>

- እናቱ - ወ/ሮ አበባዬ ገብሩ ኪዳነማርያም
- እህቶቹ -  1. ወ/ሮ እንግዳዬጥ ማሞ   2. ወ/ሪት ሸዋማሻሽ ማሞ   3. ወ/ሮ ስምረተ ማሞ  4. ወ/ሮ ምንውዬለት ማሞ
- ወንድሞቹ - 1. አቶ በሱፈቃድ ማሞ  2. አቶ ብናልፈው ማሞ   3. አቶ ገነነ ማሞ

የሁላችንም አድራሻ፡- ኢቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ፣ወረዳ 8፣አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ ነው፡፡

የተጠቀሱት ዓ.ም በሙሉ እንደ ኢትዮጵያውያን የዘመን አቆጣጠር መሰረት ነው፡፡

<u>"ረጅም ዘመን እንደመለያየታችን መልክህን ለማየት እና ድምጽህን ለመስማት አልቻልንም፡፡</u>

<u>እናም ለዘወትር ትናፍቀናለህ ስጋና ደማችን ነህ፡፡"</u>